ያ ትውልድ

የ«ያ ትውልድ ተቋም» ልሳን

ያ ትውልድ ቅጽ 10 ቁጥር 7 ነሐሴ 26 ቀን 2015ዓ.ም.

# ኢትዮጵያዊነት

*(ኢሕአፓ የታወጀበትን 48ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ)*





ዴሞክራሲያ

ቅጽ 2 ቁጥር 13 xxxxxxxxxxxxx xxxxxxxxxx ነሐሴ 21 1967 ዓ.ም.
x የኢትዮጵያ ሕዝብ ... ለበን:: x
xxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxx

የዛሬ ሶስት ዓመት ተኩል የተመሠረተና ህልውናውን በይፋ ሳይገልጽ ሲታገል የቆ
የው የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ከዛሬ ሶስት ... በፊት በተደረገው ኮንፈረ
ንሱ የሰብ አደረጃጀትና የተቀረፀውን የሠፊው ሕዝብ ትግል በይፋ በመውጣት ለማፋፋም ለ
ማቀናበርና ለመምራት ወስኗል::

ከ1964 ዓ.ም. ኢጋማሽ ጀምሮ በህቡዕ ሲንቀሳቀስ የነበረው ኢሕአፓ ነሐሴ 21 ቀን 1967 ዓ.ም. ባወጣው “ዴሞክራሲያ” ልሳኑ ቅጽ 2 ቁጥር 13 እራሱን ለሕዝብ ይፋ ያደረገበት 48ኛ ዓመት። በቀጣይ ቀናት ነሐሴ 26 ቀን 1967 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ራሱን አወጀ። ኢሕአፓ በዚህ ቀን የፓርቲ ፕሮግራሙን ያወጣውና የተሰራጨው በአማርኛ፣ በኦሮምኛ፣ በትግሪኛ፣ በእንግሊዘኛ፣ በፈረንሳይኛና በአረብኛ ቋንቋዎች ነበር።



- ይህ ፕሮግራም በኦሮምኛ በትግርኛ በእንግሊዝኛ በፈረንሳይኛና በአረብኛ ጭምር ወጥቷል::

- ጥሊ ጽሒፈ ፕሮግራሚን ኩን አፋን አማራ አፋን ኦሮሞ አፋን ትግሬ አፋን እንግሊዝ አፋን ፈረንሣ ፎ አፋን አረባ ቱ ኣካማ ጂያ ቱ::

- እዚ ፕሮግራም እዚ ብአምሓርኛ ብኦሮምኛ ብእንግሊዝኛ ብፈረንሳይኛ እውን ተሓቲሙ ኣሎ:

-This program is out also in Amharic, Oromgna, Tigrigna, French and Arabic.

-Ce programme est aussi publie - en Amharique, en Tigrigna, en Oromigna, en Anglais, et en Arabique.

أيضا وقد تم هذا البرنامج في اللغة التالية
في الأمهارية في الأرومية في التغرية في الإنجليزية
في الفرنسية وفي العربية

ለኢሕአፓ ቤተሰቦችና ደጋፊዎች እንዲሁም ለኢትዮጵያ ሕዝብ በሞላ እንኳን አደረሳችሁ መልዕክታችን ከ«ያ ትውልድ ተቋም» ይድረሳችሁ።

ኢሕአፓ “ፋኖ ተሰማራ” ብሎ የኢትዮጵያን ሕዝብ ከጭቆና ቀንበር ሊያላቅቅ “ብረት አነሳሁ፤ ለትግል ተነሳሁ” ብሎ እነሆ ወደ ገጠሪቱ ኢትዮጵያ ያቀና ቀዳሚ ፓርቲ ነበር። የኢሕአፓ መሥራች አባላት ከነበራቸው ዘመናዊ ትምህርት ደረጃ በአጠቃላይ ለግል ሕይወታቸውና ኑሯቸው ከማንም የማያንሱ ብቻ ሳይሆን በቤተሰብ ደረጃም በወቅቱ በገቢያቸው ዳጎስ ካሉ ቤተሰቦች የፈለቁ በርካታ ናቸው። መደባቸውን ለሚወዱት ሕዝባቸውና ሀገራቸው የለገሱ በርካታ ናቸው። ያስተማራቸውን ሕዝብ ሥቃዩን ሊቀርፉለት “የትግሉ ነው ሕይወቴ” ብለው ግምባር ቀደም ፋና ወጊ ሆነውለታል። ሕዝባቸውን ሊያድኑ የዜግነት መብቱን “የዴሞክራሲ መብት ያለገደብ” መፈክራቸው ዛሬም ህያው ያደርጋቸዋል። ሀገር ለሕዝብ ብለው “መሬት ለአራሹ” ጩኸታቸው ዛሬም አታጋይነቱ የነበራቸውን አርቆ አሳቢነት ያጎላዋል። “ሀዘንሽ ሀዜ” ብለው ስለ ሀገር ጮኸዋል። “ብሶትሽ ብሶቴ” ብለው ስለ ሴቶች መብት ታግለው ሴቶችን ቁራጥ የትግል እመቤት አድርገዋል፣ “ያገር ያለህ” ብለው ለብሔር/ብሔረሰቦች መብት ታግለዋል። የኢሕአፓ ታሪክ ሲነሳ መፈክሮቹ፣ ትግሉ፣ ጀግንነቱ፣ ቆራጥነቱ፣ የተከፈለው መስዋእትነት፣ ተጋድሎው፣ በተለያየ መልኩ ቃላት ቢወረወሩ የሚያደምቀው ነው። ለተፈለገው ድል ባይበቃም ታሪኩ እጅግ አስተማሪ ነውና ቢፃፍ ያኮራል፣ ቢነገር ይደመጣል፣ ቢተረክ ዓይን ዕምባ ይቋጥራል፣ ቢዘመር ስሜትን ይመስጣል።

ኢትዮጵያዊነትን ተላብሶ ኢትዮጵያዊነትን ያጎላ የኢሕአፓ ትውልድ! ትግል ዓላማ መሆኑን ያሳየ ብርቅዬ ትውልድ! ኃይልና ሥልጣን ለኢትዮጵያዊነት ያለ ትውልድ! የፍትህ ያለ ብሎ የሞገተ ትውልድ! ይህ ነው እንግዲህ አንኳር የነሐሴው 26 ቀን 1967 ዓ.ም. የኢሕአፓ ፕሮግራም።

ታሪክን በአግባቡ የመዘገብም ሆነ የመያዝ ልምዱ የለንምና ቢኖርም ቀና ቀናውን ለማየት ከመሞከር ይልቅ ደካማውን ስለምንከተል እነሆ ያን የመሰለ የአደረጃጀትና የአወቃቀር ስልት ያለውና ያስተማረ ድርጅት ሊደገም አይደለም ሊታይም አልቻለም።

ኢሕአፓ ለድል አለመብቃት ይዞት የተነሳው ዓላማና ፕሮግራም አጥፊነት ሳይሆን ዛሬ ዘር ተኮር ጭፍጨፋ እንደሚካሄደው ያኔ አንድ ፓርቲ ተኮር ጭፍጨፋ ተካሂዶበት ብቅ ባለ በሦስት ዓመት ውስጥ የከተማው መዋቅሩ በሞላ ሊመታ ችሏል። “ከእኔ በቀር ሌላ አልሰማ” ባዩ ፋሽስት መንግሥቱ ኃይለማርያም አገዛዝ በአጠገቡ በተኮለኮሉት አድርባይ ምሁሮች የጥፋት አቀነባባሪ ኃይል እገዛ እንደዛሬው ዘር ሳይለይ  ወጣት ተኮር ጭፍጨፋ ተካሂዶ ትግሉ ሊኮላሽ ችሏል።

ወጣቶች በከተማው በቀበሌ፣ በገጠሩ በገበሬ ማህበራት ክልል ተከበቡ። ሠራተኞች፣ መምህራን፣ ጋዜጠኞች በጥቅሉ የብዙኃን ማህበራት መኢሶን ለጥፋት ባዋቀረው “የሕዝብ ድርጅት ጊዜያዊ ጽሕፈት ቤት” መዳፍ ውስጥ ወድቀው መተናፈሻ አጥተው አሸለቡ።

ለኢሕአፓ የሌለውን ስም በምስጠት ተጠርጣሪ የተባሉትን እየነጠሉ በማሠር አልቆም ያለው ትግል፣ ወደ ጅምላ አፈና፣ ቤት ለቤት አሰሳ ትግሉን የማዳከምና የማከስም ሂደት ላይ በማተኮር ኢሕአፓን ለማጥፋት ቢጣርም “ፍጹም ነው እምነቴ ለትግሉ ነው ሕይወቴ” ባሉ አልበገር አባላቱ የማይነቀነቅ ግዙፍ ኃይልነቱን እያስመዘገበ መጣ። ያኔ እየቀነጠሩ በማሠር፣ በመግረፍና በመግደል የተደረገው የደርግና አጃቢዎቹ ሂደት የኢሕአፓን የመቋቋም አቅም ሊገታው አልቻለውምና ሌላኛው ምዕራፍ ቀጠለ።

ነሐሴ 21 ቀን 1969 ዓ.ም.  በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ሊቀመንበር መንግስቱ ኃ/ማርያም የሚመራ “ብሔራዊ አብዮታዊ ዘመቻ መምሪያ” በማቋቋም በከተሞች እስከ ቀበሌ በየክፍላተ ሀገር እስከ ወረዳ በተዘረጋ የደርግና መኢሶን የጋራ አወቃቀር ዘመቻ መንጥር፣ አሰሶ መደምሰስ በመላው ሀገሪቷ ይካሄድ ጀመር። ይህ ሁሉ ውርጅብኝ በኢሕአፓ ላይ የመጣው ሥልጣን ለሕዝብ በሚለው ማታገያው “ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት አሁኑኑ” በሕዝብና ወጣቱ ዘንድ ተቀባይነት ማግኘቱ፣ “የዴሞክራሲ መብት ያለ ገደብ መፈክሩ” ደርግና መኢሶንን እና አጃቢዎቻቸውን ድምጽ ስላሳጣቸው፣ ለነሱ ሀገርና ሕዝብ ማለት ሥልጣናቸው ሆነና በዘመቻ መልክ ትውልድ እምሽክ አድርገው ሀገር ዛሬ እደረሰችበት አጣብቂኝ ውስጥ ትገባ ዘንድ መሠረቱ የተጣለው ያኔ . . . ያኔ የዛሬ 45 ዓመት ገደማ ነፃ እርምጃና ቀይ ሽብር እየተባለ በተፈጀ ትውልድ ነበር።

ታሪክን እያንኳሰሱ መዘገብ ወይም የትላንቱን መካድ ለዛሬው ማንነት ሽፋን እየሆነ እና ዛሬን ብቻ እየተመለከትን ስለምንጓዝ አልታየንም እንጂ ሀገራችን ላይ ለደረሰው የዛሬ ምስቅልቅልነት ትላንት የተሠሩ ጥፋቶች ነበሩ። ኢሕአፓ ከሁሉም የተውጣጣ፣ የደርግንም ወታደራዊ አገዛዝ ጨምሮ “ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋም” ጥያቄ ምኑ አስከፊነት አለውና ነው እሥር፣ ግርፊያ፣ ግድያ የሚያስከትለው? ይህም አልበቃ ሲል በመንግሥት ደረጃ በተዋቀረ የማጥፋት ዘመቻ ብርቅዬ ትውልድ እምሽክ ብሎ መበላቱ በተጨማሪ ኢትዮጵያዊነት ላይ የሀዘን ድባብ የጣለበት ዘመን ቢኖር የደርግና አጃቢዎቹ ዘመን ነበር።

ደርግ ኢትዮጵያዊንት ብሔራዊ ስሜቱን ከሥልጣን ጋር በማቆራኘቱ ነው ኢሕአፓን አጣጥሞ ሳይጨርስ መኢሶን ላይ፣ ወዝ ሊግ ላይ የሠፈረባቸው። በቀጣይነትም ኢጭ አት፣ ኢማሌሪድ ተጣጥመው በመንግሥቱ ኃ/ማርያም በሚመራው አብዮታዊ ሰደድ መዳፍ ሥር የገባው የይስሙላ ኢማሌድን ወደ ኢሠፓአኮ ከዚያም ወደ ኢሠፓ በመሸጋገር እየተገለባበጠ ተጓዘ። በዚህ ሂደት “ከጓድ መንግሥቱ ኃይለማርያም ቆራጥ አመራር ጋር ወደፊት!” ለማስጮህ አጠገቡ ያሉትን ወታደራዊ የደርግ አባላት ሲጀምርም ያስጉኛል ያላቸውን እየበላ በኮሎኔል አጥናፉ አባተ ላይ ባደረገው የግፍ ግድያ ሁሉም ቀና ብለው እንዳያዩት ያደረገ ፋሽስት ገዢ እንደነበር ክደው ዛሬ “እሳቸው” እያሉ የራሳቸውን ኃጢያት ሊሸፋፍኑ የሚሞክሩ ስናይ ሥልጣን ላይ ያለችው ትባባስ ናትና አይፈረድባችሁም ማለት ብቻ በቂ ይመስለናል።

የ1966ቱ ኢትዮጵያዊነትና የሀገር ፍቅር ስሜት እየተደበደበ ሲሄድ ቀደም ሲልም አቆጥቁጠው የነበሩትና በተለይ በጊዜው በኤርትራ የቅኝ ግዛትነት ጥያቄ ደፈጣ ይዘው ይጠባበቁ የነበሩ ዘረኛ ድርጅቶች በሩ ወለል ብሎ የተከፈተላቸው በደርግ ዘመን “ኢትዮጵያዊነት ከእኔ በላይ ላሳር” መመሪያው ባደረገ የደርግ ጭፍን ጭፍጨፋ ምክንያት ነበር።

የአንድነት ኃይል እጅጉን ተመታ፤ ኢትዮጵያዊነት ስደት፣ ተስፋ መቁረጥ፣ አለመተማመን ሆነ። ኢትዮጵያዊነት በአንድ ማዕድ መብላት ቀርቶ የራሴን ብቻ ሆነ። ኢትዮጵያዊነት በመላው ዓለም ተበተነ። ዘረኝነት ፈነጠዘ። ደርግ ቀጥቅጦ ዝም ጭጭ

ያሰኘውን አንድነት ዘረኝነት ተጠቀመበት። ከኢትዮጵያዊነት ይልቅ ዘሩን ፈላጊ ተበራከተ። የሀገራችን ታሪካዊ ባዕዳን ጠላቶቻችን ጅምር እቅዳቸው ኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ስሜትን ማዳከም ነበርና ተሳካላቸው። እነሆ ለአለፉት 48 ዓመታት ***በኢትዮጵያዊነት የተደራጀ ፓርቲም ይሁን ድርጅት ምነዋ አልታይ አለ? ቢባል ኢትዮጵያዊነት በግል እንጂ በኅብረት እንዳይዳዝ ተደርጎ በመቀጥቀጡ ለመሆኑ መለስ ብለን የኋላውን እንቃኝ።***

የኢትዮጵያዊነት መዳከም አቅጣጫ በመያዙ በቀጣይነት ሀገራችን እንዴት ተደርጎ በዘርና ቋንቋ እንደምትሸነሸን የተጠመደልን ወጥመድ ላይ ተዘፈቅን። ኤርትራን አስገንጥሎ ሀገራችንን ወደብ አልባ ያደረገው የህወሓት ወንበዴ ቡድን የፈለገውን በደል በሀገርና ሕዝብ ላይ ቢያወርድ አይዞህ ባይ ባዕዳን ኃይሎች “ወፎ ቆመች!” እያሉ አበረታተው ለ27 ዓመት ኢትዮጵያ በአንድ በኩል ቀጣይ ኢትዮጵያዊ ትውልድ እንዳይኖራት ያለመ አገዛዝ በሌላ በኩል ዘረኝነት በመላው ሀገሪቷ ላይ ስነልቦናዊ ተጽህኖ እንዲያሳድር ሁኖ ጉዞው ቀጠለ።

“አልሸሹም ዞር አሉ” እንዲሉ ዛሬ ኢትዮጵያ ከአንዱ ዘር አገዛዝ ወደ ሌላው ተገላብጣለች። ይህ ብቻ ሳይሆን ከላይ እንዳስቀመጥነው ኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ስሜትን ከመሸርሸር ጎን ለጎን አስጊ ናቸው የተባሉ ጥቃቶች ተራቸውን ያዙ። እየተዳከሙ፣ በተንኮል እየተተበተቡ ያሉ ኢትዮጵያዊነትን አንጸባራቂና አስተዋዋቂ ጉዳዮች ውስጥ ለውስጥ ሲሸረሸሩ ከርመው ይፋ ይቀጠቀጡ ይንቋሸሹ ጀመር። የዐድዋ ታሪክና ምኒልክ በአንድ በኩል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በሌላ በኩል። ይህ ቀጣይ ሂደት የምኒልክን ማንቋሸሽ እስከ ጡት ቆራጭነት ሐውልት ቢያሠራም እንደማይሰምር ሲታወቅ ጭፍን ጭፍጨፋ ማስከተሉ የአለፈው የካቲት 23 ቀን 2015 ዓ.ም. የአድዋ ክብረ በዓል ሊረሳን አይገባም። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያንም በጠንካራ እምነቷ፣ በምእመናን ጥንካሬና በእግዚአብሔር ኃይል ሊቋቋሟት እንደማይችሉ ያለፈው ኅዳር 14 ቀን 2023 ዓ.ም. ሂደት በማስገንዘቡ ጥቃቱ ውስጥ ለውስጥ ያለማቋረጥ እየተገበረ ነው።

ወያኔ ህወሓት ያቦካውን የዘረኝነት አጀንዳ ሊጋግር የሚሞክረው የዐብይ አገዛዝ እያረረበት ቢቸገርም በዘርና ቋንቋ የተሸነሸነችውን ሀገራችንን የመጨረሻው በዘርና ቋንቋ የምትታመስ፣ የተበታተነች ደካማ ሀገር ለማድረግ እየተወራጨ ይገኛል።

በደርግ የተጀመረው ኢትዮጵያዊነትን ለሥልጣን ሲሉ መቀጥቀጥ ለዘረኝነት በር ከፍቶ የአንድነት ኃይሉ እንዳያንሠራራ ተደርጎ በመሰናከል ሀገር ትበታተን ዘንዳ የመጨረሻው እርምጃ “ኢትዮጵያ እንዳትሆን ሀገር፤ አማራን አከርካሪ መስበር” በሚል የአማራ ዘርን ለማጥፋት እነሆ የዛሬው የአንድ ዘር እልቂት ሀገራችን እያስተናገደች ትገኛለች።

ውድ ወገኖቻችን፡- የኢሕአፓን 48ኛ ዓመት እወጃ አስታከን በአጭሩ ልንገልጽ የወደድነው በቀላሉ ሊስተካከል ይችል የነበረውን ችግር እራሳችን አወሳስበንና አመቻችተን እንዴት ለዛሬ እንዳደረስነው በመጠኑ ለመጠቆም ያህል ነው። ***ኢትዮጵያዊነት ቢዳከምም ከቶም አይሞትም። ኢትዮጵያዊነት በያንዳንዱ ዜጋ ደም ውስጥ ያለ ነው። የደም ዓይነታችን ይለያይ ይሆናል እንጂ ኢትዮጵያዊነት ደማችን አንድ ነው።***

ኢትዮጵያዊነት ማለት ዐድዋ ነው፣ ኢትዮጵያዊነት ማለት ምኒልክ ነው፣ ኢትዮጵያዊነት ሃማኖታችን ነው፣ ኢትዮጵያዊነት ባህላችን ነው፣ ኢትዮጵያዊነት ማለት ሁሉም ዘራችን ነው፣ ኢትዮጵያዊነት ማለት ሁሉም ቋንቋችን ነው።

እንደ ኪንግ ማርቲን ሉተር እልም ሳይሆን እውን ነው ያለን። እልም አለኝ ሳይሆን እውነት አለኝ እንላለን። ኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ስሜት ዳግም አብቦ ኢትዮጵያ ለልጆቿ ትሆን ዘንድ በአማራው እየተከፈለ ያለው የመስዋዕትነት ተጋድሎ ሁሉንም ዘር ወደ አንድ አምጥቶ፣ ዘርና/ቋንቋን ያማከለው ክልል ዳር ድንበር ኢትዮጵያ ሆና፣ ሁሉም ዘረኝነትን አውልቆ ኢትዮጵያዊነት አጥልቆ፣ በውጭው ዓለም የተበተነው ኢትዮጵያዊነትን ተሸክመንና ሀገራችን ተሰባስበን “ኢትዮጵያችን ሀገራችን” የምንልበት ወቅት ሩቅ እንደማይሆን እውነት አለን።

የኢሕአፓ ታሪክ የሀገርና ሕዝብ ታሪክ ነው!
ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!
ፈጣሪ ኢትዮጵያን ይጠብቃት!
ያ ትውልድ ተቋም
ነሐሴ 26 ቀን 2015 ዓ.ም. (September 01, 2023)
yatewlid@gmail.com
7033004302